የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፱
አዲስ አበባ–ጥር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 29
ADDIS ABABA–30th January, 2003

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፪/፲፱፻፺፭ ዓ·ም
የኢትዮ–ቤልጅየም አጠቃላይ የልማት ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................................ ገጽ ፪ሺ፸፪

CONTENTS

Proclamation No. 312/2003
Ethio-Belgium General Development Cooperation Agreement Ratification Proclamation ........................................ Page 2072

### አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፪/፲፱፻፺፭
### የኢትዮ–ቤልጅየም አጠቃላይ የልማት ትብብር ስምምነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በቤልጅየም መንግሥት መካከል አጠቃላይ የልማት ትብብር ስምምነት ሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ·ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ ስለሆነ፣

ስምምነቱ በሚገባ ሥራ ላይ የሚውለው ሁለቱም ወገኖች በየሕገ መንግሥቶቻቸው መሠረት አስፈላጊውን ሥርዓት ከሚያሟሉበት ቀን ጀምሮ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ በመሆኑ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮ–ቤልጅየም አጠቃላይ የልማት ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፪/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO. 312/2003
### A PROCLAMATION TO RATIFY THE ETHIO–BELGIUM GENERAL DEVELOPMENT COOPERATION AGREEMENT

WHEREAS, an Agreement on General Development Cooperation between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Kingdom of Belgium was signed at Addis Ababa, on the 9th day of April, 2001;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall enter into force on the date on which both parties fulfill their respective Constitutional requirements;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 30th day of January, 2003;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the "Ethio-Belgium General Development Cooperation Agreement Ratification Proclamation No. 312/2003."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· ስምምነቱ ስለመጽደቁ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በቤልጅየም መንግሥት መካከል ሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ የተፈረመው አጠቃላይ የልማት ትብብር ስምምነት ፀድቋል።

፫· የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ስምምነቱን ሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፬· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Ratification of the Agreement*

The Agreement on General Development Cooperation between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Kingdom of Belgium signed at Addis Ababa on the 9th day of April, 2001, is ratified.

3. *The Power of the Minister of Finance and Economic Development*

The Minister of Finance and Economic Development is empowered to implement the Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 30th day of January, 2003.

Done at Addis Ababa, this 30th day of January, 2003.

GIRMA WOLDE GIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE